# የነገው ፍርሃት

october19,2009
abraham beyenne

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ መፅሐፍት ብቅ ብቀ ማለት ጀምረዋል። ከፊሎቹ የደራሲያኑ ገጠመኞች(memoir) ሲሆኑ ገሚሶቹ ደግሞ በዚሁ ጠገግ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ የተፈበረኩ ናቸው። የሻ/ል ተስፋዬ ርስቴው "ምስክርነት በባለስልጣናቱ አንደበት" ከነዚሁ ውስጥ አንዱ ነው። መፅሐፉ ለጊዜው ባለቀኖች ግልጋሎት እንዲሰጥ በይድረስ ይድረስ ተጠርዞ ለገበያ የቀረበ ይመስላል። የድርሰቱ ይዘትም የወቅቱን ባለጊዜዎች በአለፈውና በዛሬው ወንጀላቸው ነገ ሊገጥማቸው የሚችለውን ፍትሃዊ ፍርድ ከወዲሁ ለማምከን ታስቦ መፃኢውን ዕጣ ፈንታ ከመተንበይ አኳያ የነገው ፍርሃት የወለደው ድርሰት ይመስላል።

ደራሲው ፈረስ ቀይረው ከባለጊዜዎቹ ባላንጣ ጋር ጉግስ ለመግጠም የትናንት ቂማቸውን ቋጥረው ከዛሬው ባለጊዜ ጋር ራሳቸውን አቀናጅተው የቆሙ ሰልፈኛ ይመስላሉ። ሻ/ል ተስፋዬ ዛሬ ላይ ቆመው ነገን አሸጋግረው ሲመለከቱ የሚያስፈራቸው ነገር መኖሩን ከመረዳት አኳያ ይመስላል ፈረስ እንዲለውጡ የተገደዱት። የነገውንም ፍርሃት ከሚጋራቸው አካል ጎን ቆመው "ምስክርነት በባለስልጣናቱ አንደበት" ብለው ፅፈዋል።የድራማውና የጊዜው ግጥጥሞሽ ደግሞ በስሌት የተቀናጀ መሆኑ ዕውነትም….. እንዲሉ አንባቢን ያስደምማል።

ጊዜ መስታዎት ነው። በጊዜ ሁሉም ነገር ፍንትው ብሎ ይታያል። የጊዜ ዋጋም ክቡርነቱ ጎልቶ የሚታወቀው በራሱ በጊዜ ነው። ሕዝብ የኑሮውንና የህይዎቱን ጎዳና ደስታውንም ይሁን ሀዘኑን የሚጓዘው በጊዜ ጎዳና ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የትናንት ሰቆቃውን በጊዜ ሂደት እንዲጠግግ አንገቱን ደፍቶ በተቀመጠበት ወቅት ሻ/ል ተስፋየ ቁስሉ እንዳይሽር መነካካት ጀምረውታል።

"……time is a transparent medium. People and cities rise out of it, move through it, and disappear back into it. It is time that brings them and time that takes them away.

The understanding that says, 'This is my time' or No, this is no longer our time.' Time flows into a man or State, makes its home there and then flows away; the man and the State remain, but their time has passed. Where has their time gone? The man still thinks, breathes and cries, but his time, the time that belonged to him and to him alone, has disappear.

There is nothing more difficult than to be a stepson of the time; there is no heaver fate than to live in an age that is not your own. Stepsons of time are easily recognize: in personal departments, …….Time loves those it has given birth to itself: its own children, its own heroes, its own laborers Never can it come to love the children of the past age, any more than a woman can love the heroes of the past age, or a stepmother love the children of another woman. Such is time: everything passes, it alone remains; everything remains, it alone passes. And how swiftly and noiselessly it passes. Only yesterday you were sure of yourself,…a son of
the time. But know another time has come- and you don't even know it." (Vasily Grossman Life and Fate).

በየትም ቦታ ይሁን በየት በማንኛውም መንግስት ሥር ባገዛዙ የጋረነ ምጣድ ሲጠበስ ዘወትር ሲያርና ሲጨስ የሚስተዋለው ሕዝብ ነው። ሕዝብ ግን እንደ ታሪክ ሰሪነቱ የራሱን ታሪክ ራሱ አይፅፍም። ባለመፃፉም ዘወትር የግለሰቦች የታሪከ መድረክ ሆኖ ይኖራል። የራሳቸውን ታሪከ (memoir) መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች ብቻ በመሆናቸው የግለሰቦች ታሪክ በምንም መልኩ የሕዝብ ታሪክ ተደርጎ ሊወሰድ አይቻለውም። ሕዝብና ታሪክ ግን ምንጊዜም ሠሪና ተሠሪ ሆነው ሲኖሩ

ብዙ ዘመናት ተፈራርቀውባቸዋል።

ስለ ዘመን መፈራረቅ ካነሳን ዘንድ "ጊዜ ግልፅነት ያለው መገናኛ ነው። በጊዜ ሂደት ውስጥ ሕዝብና ከተሞች ይነሳሉ፤በውስጡም ይኳዛሉ መልሰውም በጊዜ ቀመር ይጠፋሉ። ጊዜ እንደወለዳቸው መልሶ ያጠፋቸዋል። የጌዜ ግንዛቤ 'ይህ ጊዜ የኔ ጊዜ ነው ወይንም የለም ይህ ጌዜ የኛ ጊዜ አይደለም' እንዲሉ ጊዜ በሰው ልጆች ወይንም በሃገር ውስጥ ፍሰት አለው።መልሶም ወደ ውጭ ሲከነበል የሰው ልጆችና ሃገር ይቀራሉ።ጊዜአቸው ግን ጥሏቸው ሄዷል።ጊዜ የከዳው ሰው ቅሬቱ አስትንፋሱና እለቅሶው እንጅ የኔና የኔ ብቻ ይለው የነበረው ጊዜው ከስሟል። የጊዜ የእንጀራ ልጅ እንደ መሆን አስከፊ ነገር የለም" የሚሉት ሩሲያዊ ፀሃፊ ቫዝሊ ግሮስማን " በሰው ጊዜ እንደመኖር የሚከብድ ነገር የለም።በጊዜ የከበረ ሁሉ መልሶ በጊዜ ይከስራል። ጊዜ የራሱን ልጆች፤ ጀግኖችና (heroes) የራሱን ሠራተኞች እንጂ የሚያፈቅረው ሌላው ጊዜ ስለ ወለደው ስለ አለፈው ጊዜ አይጨነቅም። ሁሉም ነገር ያልፋል። የማያልፈው ጊዜ ነው።ሁሉም ነገር ሲኖር እርሱ ብቻ ያልፋል። በጊዜ ስሌት ቆሞ የሚኖር ነገር የለም። ጊዜው ሲኖር ይኖራል ጊዜው ሲያልፍም አብሮ ያልፋል። ስለትናንቱ አንተነትህ ብቻ ነው እርግጠኛ መሆን የምትችለው። ዛሬ ሌላ ቀን ነው:: መምጣቱን እንኳ አታውቀውም። ሲሄድም ሳታውቀው ያለ ምንም ኮሽታ ጥሎህ ያልፋል" ሲሉ ያስገነዘቡት ቁምነገር ኢሠፓን ለመሰሉ ወገኖች አስተምሮነቱ በዋጋ የሚተመን አይሆንም። ኢሠፓዎች የራሳቸውን ቀን ጨርሰው ዛሬ ደግሞ ከባለቀኖቹ በተዋሱት ጊዜ የትናንት ውዝፋቸውን ሊጨርሱ ሰይፍ መዝዘው ሲወራጩ ይስተዋላል። "ጊዜ የሚያፈቅረው የራሱን ልጆችና ጀግኖች እንጂ ሌላው ሰለ ወለደው ጊዜ አይጨነቅም" እንዳሉት የሩሲያው የብዕር ሰው የትናንቱን ጊዜ ዛሬ ወይም ነገ እንዲመለስ መመኘት ናፍቆት ከመቀስቀስ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም። ቀናቸው ጥሏቸው የሸሸው ሻምበል ተስፈሰዬ ግን ከዚህ ግንዛቤ ዕርቀው ትረካ ውስጥ የገቡት አንድም ሊደብቁት አለያም ሊሸሹት የሚፈልጉት ነገር ያለ አስመስሎ እንዲሰማው ትረካቸው አንባቢን ይጋብዛል።

ለምሳሌ በገፅ 9 "ደርግ ሕዳር 14 ቀን 1967 እነ አክሊሉ ሀብተወልድን በማረድ የጭካኔ ድርጊቱን ጀመረ። ቀጥሎም ከመኢሶን ከኢሕአፓና ከራሱ ከወዝሊግ አባላት በሚሰጠው መርዛማ ምክር በመመራት ጭፍጨፋውን ገፋበት" ተብሎ የተተረከው አሉባልታ ከዕውነታው ጋር በፍፁም አይገናኝም። ደርግ እንቅስቃሴውን ሲጀምር "ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል መፈክር ነበር። ሳይውል ሳያድር ግን "ያለ ደም ሥርየት የለም" ብሎ የቀድሞ ባለስልጣናትን ገደለ። በዚህ ወቅት ኢሕአፓ እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም "ጠመንጃው ያለው በእጃችሁ ነው" በሚልበት ቅርበት በደርጉ ዙሪያ ሳይኖር "መርዛማ ምክር" እንደ ሰጠና እንዳስጨፈጨፈ ተደርጎ ተወንጅሏል። ከዚሁ ጋር በማያያዝም "በፍርሃትና በጭንቀት ማጥ ውስጥ የገባው መኢሶን ሲባዝን ሳለ በሻቢያ የተመራው የኢሕአፓ ነፍሰ ገዳይ ቡድን በመንግሥቱ ሃይለማርያም ላይ የግድያ ሙከራ በማድረጉ በደርግ ውስጥ የመንግሥቱ ሃ/ማርያም ደጋፊ የነበረው ቡድን ከመኢሶን ጋር እጅና ጓንት ሆኖ በኢሕአፓ ላይ ቅጥ የለሽ ጭካኔ ጀመረ" ተብሏል።

ይህ ሰበባዊ ምክኒያት በናዚው ዘመን በዶ/ር ጎብልስ የተፈፀመውን ተመሳሳይ ወንጀል አስታወሰኝ። ወቅቱ ሂትለር ወደ ስልጣን ለመውጣት የሚፈራገጥበት ወቅት ነበር። ሆኖም የሂትለርን ስልጣን መያዝ አጥብቀው የሚቃወሙ ሶሻሊስቶችና ኮሚኒስቶች ሂደቱን አልጋ ባልጋ ሊያደርጉለት አልቻሉም። ሂተለርም ተቃዋሚዎቹን ጭጭ የሚደርግመበትን መንገድ ሲያፈላልግ ለዶ/ር ጎብልስ አንድ

መፍተሄ አንዲሻ ጠየቀው። ባረመኔነቱ ከሂትለር የማይተናነሰው ዶ/ር ጎብልስ ተቀናቃኞችን ለማጥፋት ከፍተኛ ወንጀል ሊያስፈፀማቸው ፈለገና ቤተመንግሥቱን በሳት ለማጋየት ወሰነ።

በዕለተ-መዳህኔዓለም ጥር (feburuary) 27 ቀን ነበር የሪችስታንጉ ቤተመንግስት በእሳት የጋየው። በዚሁ ዕለት አመሻሹ ላይ እራት በዶ/ር ጎብልስ ቤት እንዲሆን ተወሰነ። ሂትለርም የለቱ ዕንግዳ ሆኖ ተጋበዘ። ዕራት ዘጠኝ ሰዓት ላይ እንዲሆን ተመቻቸ። ለዚሁ ምሽት የሚሆን ሙዚቃም ተከፍቶ ሁለቱ ጭውውት ላይ እንዳሉ የዶ/ር ጎብልስ ስልክ ጫደረ። ቤተመንግስቱ በሳት መጋየቱን ሪፖርት ለመድረግ ዶ/ር ሃንስቴግልስ ነበር የደወለው። ዶ/ር ሃንስቴግልስ ቃጠሎውን ለሂትለር ለመናገር ስለከበደው ወደ ዶ/ር ጎብልስ መደወሉ ነበር። ስለሁኔታው ወሬ አሻትቶ

በመጨረሻም ዕውነቱን አረጋግጦ መደወሉን ለጎብልስ በጥሞና አስረዳ። ዶ/ር ጎብልስም ቃጠሎውን ለሂትለር ተናግሮ ተያይዘው ወደሚነደው ቤተመንገስት ሲከነፉ ደረሱ።ቤተመንግስቱ ዕውነትም ይጋይ ነበር። ሁለቱም የእሳት አደጋውን ቱቦ እየዘለሉ ቋያውን እሳት ተረማምደው በሁለተኛው በር በኩል ወደ መሃል ዘለቁ። ጎሪንግ ዘግይቶ ተቀላቀላቸው። በዚህ ወቅት ጎብልስ በድርጊቱ የተበሳጨ መስሎ "ይህ ሴራ የኮሚኒስቶች የመጨረሻው ፀ-ረ ህዝብ ሙከራ ለሞሆኑ ጥርጥር የለውም። እነዚህ ፀረ ህዝቦች በሳት አደጋው የሚፈጠረውን ግርግር ተጠቅመው ስልጣን ለመጨበጥ የወሰዱት ዕርምጃ ነው" ሲል ሁኔታውን አክብዶ ለሂትለር ተናገረ። ፊቱንም በውሸት ንዴት ሸፈነው።ሂትለር ግን ነገሩን እንዳልሰማ ሰምቶ ምንም ነገር ትንፍሽ ሳይል ጎብልስን አስከትሎ ወደ ቢሮው ሲገሰግስ ደረሰና ለጋዞጦች ኢዲተሮች የማያወላዳ የበቀል ዕርምጃ መወሰድ እንደሚኖርበት እንዲፅፉ ትዕዛዝ አሰተላለፈ። የዚያ ቃጠሎ ጠንሳሾች ጎብልስና ጎሪንግ ነበሩ። ሂትለር ስለሁኔታው አያውቅም። ሁለቱ የሂትለር ቀኝ እጆች ጎብልስና ጎሪንግ ኮሚኒስቶችን ለማጥፋት በጎነጎኑት ሴራ ነበር ቤተመንግስቱ በሳተ የጋየው። እሳቱ እንዴት ተነሳ?

በካርል አርነስት የሚመራው የደህንነት ቡድን የፕሬዘዳንቱን ቤተመንግሥትና የሪችስታንጉን ቤተመንግሥት ህንፃ በሚያገናኘው ኮሪዶር መተላለፊያ ወደ ቤተመንግሥቱ ዘልቆ የቢሮ ወንበሮችንና ጠረጴዛዎችን ከሳት ማቀጣጠያ ኬሚካል ጋር አዘጋጅቶ ወጣ። ቀጥሎም የአእምሮ በሽተኛ የነበረው ወጣት ቫንደር ሉቤ (የኮሚንስት ፓርቲው አባል) እሳቱን ለኩሶ በሚጋየው ቋያ መሃል ከፊል እርቃኑን
ቆሞ ተገኘ። ቫንደር የደህንነቱን ሴራ የፈፀመ ወዶ ገብ ወንጀለኛ ሲሆን ድርጊቱንም የፈፀመው ዝነኛ ሰማዕት (martyrdom) ለመሆን በነበረው ምኞት እንደነበር በሰጠው ቃል አረጋግጧል። ዶ/ር ጎብልስ ከደህንነቱና ከጎሪንግ ጋር በመመሳጠር ትልቁን ቤተመንግስት በሳት አጋይቶ ኮሚኒስቶች የፈፀሙት
በማስመሰል በብዙሃን መገናኛ ወሬውን ጫፍ እስከ ጫፍ አዳረሰው። ህዝቡም ዜናውን እንደሰማ አገር ይቅር የማይለው ብሔራዊ ክህደት ተፈፀመ ብሎ ድርጊቱን በማውገዝ ከሂትለር ጎን ተሰለፈ። ኮሚኒስቶች ባልፈፀሙት ወንጀል በሃሰት ተወንጅለው ባደባባይ ተጨፈጨፉ። በዚህ መንገድ ጀርመኖች ሳያውቁ የራሳቸውን አጥፊ ሂትለርን ወደ ስልጣን አወጡ። ሻ/ል ተስፋዬ ርስቴም እንደ ጎብልስ የደርጉን ተቀናቃኝ ኢሕአፓን በፈጠራ ወንጀል ለማጥፋት "በመንግስቱ ላይ የግድያ ሙከራ ሳቢያ መኢሶን ከደርግ ጋር እጅና ጓንት ሊሆን ቻለ" ሲሉን ድፍረት አግኝተዋል። መኢሶን ከደርግ ብብት ሮጦ የተደበቀው ገና አውሮፓ እያለ ነበር። ምንም እንኳ ባይተኩስ ኢሕአፓን "መግደል" የጀመረው ገና አገር ቤት ሳይገባ አውሮፓ እያለ ነበር። በመኢሶንና በኢሕአፓ መስራች አባላት መካከል ብዙ ውይይቶች ተካሂደው መኢሶን በሚፈለገው መንገድ የነብርሀነ ቡድን መሄድ ባለመቻሉ መኢሶን አኩርፎ አቄመ። ቂሙንም መበቀል ፈለገና ቤሩት ውስጥ ወደ ፍልስጤም ሊሄድ የተዘጋጀውን የኢሕአሠን ቡድን የስም ዝርዝር ለደህንነቱ አሳልፎ ሰጠ። ደርግም ውለታውን ለመክፈል ይመስላል ለያንዳንዱ የመኢሶን አባል የአየር ትኬት በመላክ ወደ አገር ቤት እንዲጉቡ አጓጓዛቸው። እነርሱም ራሳቸውን ችለው መታገል እንደማይችሉ ተገንዝበው "ሂሳዊ ድጋፍ" በሚል ሽፋን ወደ ደርግ ብብት ገቡ። የደህንነቱ ባልደረባ ሻ/ል ተስፋየ ይህንን ሃቅ ግጥም አድርገው እያወቁ "በመንግስቱ የግድያ ሙከራ ሳቢያ መኢሶንና ደርግ እጅና ጓንት እንደሆኑ ዋሽተውናል።

ሁለቱ ፀረ-ህዝብ ሃይሎች ከመንግስቱ የግድያ ሙከራ በፊት ገና አብዮቱ እንደፈነዳ በ1967 ዓ ም ነበር እጅና ጓንት ሆነው መግደል የጀመሩት። ጊዜውን ወደ ሁዋላ መለስ ብለን በምናባችን ስንጎበኘው ጊዜ በባድማው አስቀምጦ የሚጠብቀን ራሱን በራሱ ገላጭና ጉልህ አሻራ አለው። ደርግና መኢሶን በኢሕአፓ ላይ ግልፅ ጦርነት ያወጁት በኖቬምበር 1968 ዓ ም ነበር። ደርግ ስልጣኑን እንደጨበጠ ለሕዝብ እንዲያስረክብ ከያቅጣጫው ውትወታ ነበረበት። ደርግ ግን የተጠየቀውን ጥያቄ የመለሰው በሃይል አፀፋ ነበር። ሆኖም እኒያ በየካቲት አብዮት ግንባር ቀደምትነት ተሳታፊ የነበሩ ሁሉ አምርረው ተቃወሙ። በዚህም ሳቢያ የላብ አደሩና የተማሪው ማህበራት መሪዎች ዕየታደኑ ታሰሩ። በወታደሩ በኩል የተነሳውንም ተቃውሞ ለመግታት ከ4ኛ ክፍለ ጦር በተላከው ቡድን የመሃንዲስ ክፍል ጥቃት ደረሰበት። አምስት ወታደሮች ተገደሉ።ሰባት

ቆሰሉ። ከሃያ በላይ የሚሆኑት ከአርሚ አቪየሽንና ከክቡር ዘበኛ ታፈሱ። ከገንዘብ ሚኒስቴርና ከሌሎች መ/ቤቶች ከ30 በላይ ምሁራን በርጌሶች(ሲቪልስ) ታሰሩ። ቀጥሎም ከማሰር ወደ መግደል ሂደቱ ተሸጋገሮ፦

ህዳር 14 ቀን 1967 ዓም የቀድሞ ባለስልጣናት በጅምላ ተረሸኑ። መጋቢት 1967 ዓ ም ብርጋዴር ታደሰ ብሩ፤ ኮ/ል ሃይሉ ረጋሳ፤ደጃች አሉላ በቀለ፤ መለስ ተክሌ፤ ግደይ ገ/ዋህድና እረዘነ ሀጎስ ዕድሜ ይፍታህ ተፈረደባቸው። ቆይቶ ግን የዕድሜ ይፍታሁ ፍርድ ተሽሮ ሁሉም ተረሸኑ።

መስከረም 27 1967 ዓ ም(ኦክቶበር 7 1975) በመሃንዲስ ክፍሎች ላይ ጥቃት ደርሶ ሃ/ቃ መንግስተ-አብ ሀይሌ፤ምአ/ቃ ብርሃኑ መሃሪ፤ ጣሰው ሃይለ ሚካኤልና ወልደ ሚካኤል ከበደ ተገደሉ።ሻ/ቃ የታየው ቦርቂሳ ሃም/ቃ በቀለ ቱሉ ምአ/ቃ ወ/ጊወርጊስ ታቱ ምአ/ቃ ስነታየሁና ሌሎችም ባለሌላ ማእረግ ወታደሮች ቆሰሉ። ጥቅምት 17 ቀን 1967 ዓ ም(ኦክቶበር 23) ሰላማዊ ስብሰባ ባደረጉ ሥራ አጦች ላይ የፀጥታ ሃይሎች ተኩስ ከፍተው አንድ ሰው ገደሉ።

ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ ም (ማርች 13) ሌተ/ል አማረ በሽንን ጨምሮ አራት ሰዎች በወበራ ወረዳ ሰላሌ አውራጃ በፀጥታ ሃይሎች ተገደሉ።

ሚያዚያ ወር የሁለተኛና የሶስተኛ ክ/ጦር የጊዙ ገደብ ሰጥተው ደርግ ስልጣኑን ለሕዝብ እንዲያስረክብ በመጠየቃቸው የግፍ ዕርምጃ ተወስዶ ከ35 የላነሱ መኮንኖችና ወታደሮች ተገደሉ። ዶልታችሁዋል በሚል ሰበብ ሌተ/ል ንጉሤ ሃይሌንና ደበሱ በየነን ጨምሮ ብዙዎች ታሰሩ።

ሚየዚያ 22 1967 ዓ ም(አፕሪል 30 1975) ሰላሳ አርሶ አደሮችና የገበሬ ማህበራት መሪዎች በከፋ ክ/ሀገር የቡና ሊሙ ውስጥ ዘጠኝ፣ ጊምቢ ወለጋ ውስጥ ስድስት፣ ኖጳ ኤሉባቡር ውስጥ ቁጥራቸው በርካታ ሰዎች ተገደሉ። በዚሁ ጊዜ ደረጀ ለገሰ የተባለ ምሁርና ሌሎችም ሊሙ ከፋ ውሰጥ ተረሽነዋል። ብቸና ጎጃም ውስጥ በሻ/ቃ እንዳለ ተሰማ (የኢሠፓ ማኮ አባል) በተመራ ጭፍጨፋ ከአንድ ሺህ የበለጡ አርሶ አደሮች ተገድለዋል። አርሶ አደሮቹ የተገደሉት በሞርታርና በሄሊኮፕተር ጋንሽፕ ነበር። በዚሁ ግድያ ወቅት በጣም ወጣት ወንድማማቾች ምኒልክና ግርማ ገሠሠ አከለ ስንኩሉ አቶ ውበት፤ አቶ አደምና የጠጠሱት ሽመግሌ አባ ዑመር ይገኙበታል።እንዲት ሴትዮም ከሰባት ልጆቿ ጋር በጎጆዋ ውስጥ እንዳለች በዕሳት ጋይታ ሞታለች።

በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞችም ውስጥ ሜይ ደይ በተከበረበት ዕለት ከሃያ አንድ የማያንሱ ሠራተኞችና ተማሪዎች ሲገደሉ ሌሎችም ተይዘው ታስረዋል።

ከግንቦት እስከ ሰኔ 1967 ዓ ም የተማሪዎች መነሳሳት እየተስፋፋ ሄዶ በተደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች አስራ አንድ ተማሪዎች ተገድለዋል። ግንቦት 30 1967 ዓ ም (ጁን 7 1975) ጦቢያ ይጥኔ ጋሹ ክፍሌ ሞገስ ወርቁ ስዩም ዘርዑ ሃይሌ ዕድሪስ ኪየር አበዱልቃዲርና ወታደር ጌታቸው ፋነታዬ በይፋ ተረሽነዋል።

በሰኔ 8-9 1967 ዓ ም (ጁን 15-16 1975) ወላይታ ውስጥ የፀጥታ ሃይሎች የሚያደርሱባቸውን ሰቃይ ስለተቃወሙ ብዙ ሰዎች የግፍ ዕርምጃ ተወስዶባቸዋል። የቆሰሉና የታሰሩም ነበሩ። በሰኔ 22 1967 እና በሃምሌ 1 1967 ዓም መካከል(ጁን 8-22 1975) ቀናት ብቻ መንግሥቱ ሀ/ማርያም ባቀረበው ዘገባ ከልዩ ልዩ ቦታዎች ከስድሳ አምስት የላነሰ ቁጥር የነበራቸው ሰዎች ተገድለዋል። ቦንጋ ውሰጥ (ከፋ ክ/ሀገር) በዚሁ ዓመት 150 አርሶ አደሮች ተገድለዋል። በገለታ (ፈለገ ንዋይ) ውስጥ (ጋሙ ጎፋ) በአንድ ቀን 80 ሰዎች ተገድለዋል።

ነሃሴ 26 ቀን 1967 ዓም ኢሕአፓ ፕሮግራሙን በሶስቱ ዋና ዋና የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በመላው ኢትዮጵያ በማሰራጨት ህልውናውን ሲያሳውቅ መንግሥቱና መኢሶን ይበልጥ ተርበደበዱ። የሁለቱ እጅና ጓንት መሆን ተጠናክሮ ዕርምጃው በስፋት ቀጠለ።

ከኢሕአፓ ልደት ቀጥሎ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በመስከረም ወር 1967 ዓም ጉባኤውን ጅማ ውስጥ በማካሄድ ቀደም ሲል በሰኔ ወር 1967 ዓም አስተላልፏቸው የነበሩትን ጥያቄዎች እንደገና በሚያስተጋቡ ውሳኔዎች ወስኖ በውሳኔውም የሚፈፀመው ግፍ እንዲቆም፤ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ፤ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፤

ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሠረት በውሳኔው ጠየቀ።ደርግም መምህራኑን "አድሃሪያን" በማለት የተመረጡትን መሪዎች አሰረ። መስከረም 17 ቀን1968 ዓም በመምህራኑ ላይ መግለጫ አወጣ። መግለጫው "የሃገርን አንድነት ለማናጋት ሕዝብን በሃይማኖትና በጎሳ በመከፋፈል በመካሄድ ላይ ያለውን አብዮት ለማጨናገፍ ሞክረዋል" የሚል ሲሆን በዚሁ መስከረም ወር ላይ የሠራተኞች ማህበርም ጉባኤ አካሂዶ የጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥትን ጠያቄና ሌሎችንም የህዝብ ጥያቄዎች ጠየቀ። ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተሰጠው መልስ ግን እስራትና ግድያ ነበር።

ደርግ በወቅቱ የገጠመውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ለማፈን ያስቸኳይ ጌዜ አዋጅ በማወጅ ግድያውን አባባሰው።ኢወማ ተዘጋ። መሪዎቹም "የኢምፔሪያሊስት ቡችሎች" እየተባሉ ታደኑ። የደርግ መንግሥት በጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲተካ የጠየቁ ተረሸኑ። የተማሪዎች፤ የመምህራን የሠራተኞች መህበራትና ኢሕአፓ "የሕዝብ ጠላቶች" ተብለው በመኢሶንና በደርግ ታሰሩ። ተፈጳዩ። ተገደሉ።

በዚህ ወቅትም ነበር የመኢሶኑ ሊቀ መንበርና ስዊድን አገር የተማረው ከበደ መንገሻ 'ከቤት ቤት ፍተሻ' ማካሄድና 'አዲስ አበባን ከ አናርኪስቶች ማፅዳት' እደሚያስፈልግ  ለደርግ ማስታዎሻ የፃፈው። ቀጥለውም የወዝ ሊጉ መሪ ዶ/ር ሰናይ ልኬና ከበደ መንገሻ ያሰናዱት 'የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች' የስም ዝርዝር ጋዜጣ ላይ ወጣ። ከዚህ ድርጊት ተከትሎም ደርግ የካቲት 24 ቀን 1968 ዓም (ማርች 3 1976) ሽብር ከፍቶ የኢሕአፓን ታጋዮችና ደጋፊዎች ለመጨፍጨፍ ማቀዱን የሚገልፅ መግለጫ አወጣ። በእቅዱም መሰረት በሻ/ቃ አሊ ሙሳና በሻ/ቃ ጌታቸው ሽበሺ መሪነት የተንቀሳቀሰው የፀጥታ ሃይል በከፋ፣ በሐረር፣ (አሰበ ተፈሪ) አዋሽና ወልቂጤ ተዘዋውሮ መግለጫውን በተግባር በመተርጎም በኢሕአፓ ላይ ቅጥ የለሽ ግድያ አካሄደ።

በሃምሌ ወር 1968 ዓም ሁለቱ ሻለቆች በስምሪታቸው ግድያውን ሲያጧጥፉ ጎን ለጎን በሻለ/ቃ ታከለ ወልዴ የሚመራ ቡድን በሲዳሞ ክ/ሀገር አፈሮ ውስጥ 200
አርሶ አደሮችና ዘማች ተመሪዎችን ጨፈጨፈ። ነሃሴ 1968 የደርግ አረመኔ ባህሪይ እርቃኑን ቆሞ ለዓለም ራሱን አጋለጠ። "ደርግ ለወዳጁ እሳት ይዟል በእጁ" እየተባለ ቅጥ ያጣው ግድያ አገሪቱን በደም ጎርፍ አጥለቀለቃት። የባቢሌ ቶላን አንድ ትውልድ ለመምተር ይመለከቷል።

ኢሕአፓም የአልሞት ባይ ተጋዳይነት የመከላከል ትግል የጀመረው ከዚህ ሁሉ የደርግና የመኢሶን ጭፍጨፋ በሁዋላ ነበር። በመሆኑም መስከረም 12 ቀን 1969 ዓም መንግሥቱ ሃ/ማርያመን ለመግደል ሙካራ አደረገ። መስከረም 14 ቀን 1969 ዓም በፍቅሬ  መርዕድ ላይ ዕርምጃ ወሰደ።አንባቢም ከዚህ ሃቅ ተነስቶ፦
ሀ. የመጀመሪያውን ጥይት ያጮኸው ኢሕአፓ ነበር? ወይስ ደርግና መኢሶን?
ለ. የመጀመሪያውንስ የመንገድ ላይ ግድያ ፍቅሬ መርዕድን በመምታት        የጀመረው ኢሕአፓ ነበር?
ሐ. መኢሶንና ደርግስ እጅና ጓንት ሆነው ቅጥ የለሽ ግድያ በኢሕአፓ ላይ የፈፀሙት ደራሲው እንደሚሉት በኮ/ል መንግስቱ ላይ የግድያ ሙከራ ከተደረገ በሁዋላ ነበርን? ብሎ ራሱን እንዲጠይቅና የህሊና ዳኝነቱን እንዲሰጥ ይጠበቅበታል።

የሞት ትንሽና ትልቅ የለውም። ፍቅሬ መርዕድ ከመሳፍንት ቤተሰብ ስለተወለደና የፈረንሳይ አገር ያውም የፓሪስ ምሁር ስለነበር ሌሎች ግን ካጣ ከነጣ
ድሃ ቤተሰብ የመጡና የትምህርት ደረጃቸውም ዝቅተኛ በመሆኑ የፍቅሬን ሞት የመጀመሪያ ሞት ሊያደርገው አይችልም። ለሟች ወገን ሃዘኑ አይበላለጥም። እኩል ነው። ኢሠፓዎችም በዚህ ጉዳይ ላይ የስውን ጩኸት ቀምተው ስለጮሁ ጩኸታቸው ከወንጀል ነፃ አያድርጋቸውም። ኢሕአፓንም በሀገር ክህደት ወንጀል ለመወንጀል ከአልጄሪያና ከጀርመን የስለላ ድርጅቶች ጋር ማዛመዱ የንፁህ ስወነት ካባ አይደርብላቸውም።

ኢሕአፓን ያልጀሪያና የጀርመን የስለላ ድርጅቶች ጉዳይ አስፈፃሚ ለማስመሰል "ያልጀሪያ የውጭ መረጃ ድርጅት እነ ብርሃነ መስቀልን እረድቶ ለኢሕአፓ ምሥረታ አብቅቷቸዋል" ሲሉ ኢሕአፓ በወቅቱ ላልጄሪያ መንግሥት ሊሰጠው የሚችል ምን ዐይነት ግልጋሎት ሊኖር ይችላል? የጀርመን የስለላ ድርጅትስ ለኢሕአፓ መመስረት አስተዋፅዖ ማበርከቱ ለምን ግብዓት ነበር? ብሎ

መጠየቅ አግቦነት ይኖረዋል። እንደሚታወቀው ዘመኑ በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ የአፍሪቃ አገሮች ነፃነታቸውን ለማግኘት ይጋደሉበት የነበረበት ወቅት ነበር። አልጀሪያም ከቅኝ ገዥዋ ከፈረንሳይ ጋር እልህ ያስጨረሰ ትግል አካሂዳ ነፀነቷን ያወጀችበት ወቅት ነበር። ከነፃነት በሁዋላም ግንኙነቷን ከምስራቁ ጋር አቀራኝታ በምዕራቡ ዓለም የጎሪጥ ከሚታዩት አገሮች አንዷ እንድትሆን አቋሟ ጠላት አፍርቶባት ነበር። ይልቁንም እንደ እርሷ የምዕራቡን ካፒታሊዝም ተቃውማ ባሜሪካ አፍንጫ ስር ከቆመችው ከኩባና ከቼ ጉቬራ ጋር የጠነከረው ግንኙነቷ በምዕራቡ ጥርስ አስገብቷት እንደ ነበር የደህንነቱ ቢሮ አያውቅም ብሎ መገመት ያስቸግራል። ቼ ጉቬራም በምዕራቡ ጥርስ ውስጥ ገብተው ይታኙኩ ከነበሩት ኮሚኒስቶች አንዱና ዋነኛው ስለ ነበር ያልጀሪያው የግራ መንግስት ዕድሜው ባጭር ሊቀጭ ችሏል። ዓለም በዚህ ሁኔታ በነበረችበት ወቅት ያልጄሪያና የጀርመን የስለላ ድርጅቶች ኢሕአፓን ለመመስረት ፈጠሩት የተባለው ትብብር የዶ/ር ኀብልስንና የደህንነቱን የፈጠራ ሥራ ከማጎላት ሌላ ትረካው ትርጉም እይኖረውም። የሆነ ሆኖ ግን ያልጀሪያ መንግስት ለነ ብርሃነመስቀል ጥገኝነት የሰጠበት ምክኒያት
ነበረው ብሎ ለማመን የሚያስችል ሁኔታ ነበር። እነ ብርሃነ ማርክሲስቶች ነበሩ። አልጀሪያም እንዲሁ። የማርክሲዝም ዓለማቀፋዊ ወንድማማችነትም (ኮሚንተርን) በሩሲያ መሪነት ህልውናውን አስመዝግቦ ነበር። የነብርሃነ ቡድንም ካልጀሪያ መንግስት ጥገኝነት የመሰጠቱ ጉዳይ የማርክሲዝም ርዕዮት የፈጠረው ትብብር እንጂ ደራሲው እንደሚሉት ለፔትሮ ዶላር ጥቅም አስጠባቂነት ኢሕአፓ አልተመሠረተም። ከዚህም ሌላ አልጄሪያ በወቅቱ ከጀርመን ጋር የምተጋራው የስትራቴጂክ ጥቅም ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበራትም።ሻ/ል ተስፋዬ ባንድ በኩል ኢሕአፓን "የፔትሮ ዶላር ቅጠረኛ" ለማስመሰል ሲጣሩ በተፃራሪው ግን ፀረ-ዐረብ ከነበረችው ጀርመን ጋር አዛምደውታል። ይህንንም ሆድና ጀርባ የሆነ ግንኙነት አስመሳይ ቀለም ቀብተው ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳን ያለ ቦታቸው ለምስክርነት ጠርተወቸዋል።

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋሞች የሌኒን ቀይ ጦር ከዛሩ መንግስት በተሰነዘረበት ጥቃት የመበታተን አድል እንዳይገጥመው ካቲታሊስቶቹ ከሚሊዮን በላይ ዶላር ለነሌኒን አበድረው ቀዩን ጦር ካደጋ መታደጋቸው አይዘነጋም። ሻ/ል ተስፋዬ አለወቁት እንደሁ እንጂ እነዚህ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቐሞች ማኦንና የቻይናን ኮሚኒስት ፓርቲ እረድተው የቬትናምንም ጦርነት አወግተዋል። ያሜሪካውን
የርስበርስ ጦርነትም ደቡቦቹን እረድተው ጦርነቱን ያስጀመሩት እኒሁ ባንኮች ነበሩ። ባንኮቹ የእርዳታቸውን ግብዐት የሚያዩት ከትርፍና ከወለድ አኳያ እንጂ ከሌላ ነገር አኳያ አለመሆኑ የፖለቲካ ሀ...ሁ ነው። ባንኮቹ ለሌኒንና ለማኦ እጃቸውን የዘረጉት የሁለቱ አገሮች የሩሲያና የቻይና የወደፊት እድገት ከግሎባል የገንዘብ ትስስር ጋር ሚኖረውን እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ አጢነው ነበር። ታዲያ የጀርመኑ የስለላ ድርጅት ኢሕአፓን መርዳት የፈለገው ለዚህ ግብዓት ነበር እንዳይባል የዛኔዋ ኢትዮጵያ ለግሎባል ንዋይ ፍሰት የምትታጭበት የኢኮኖሚ እድገት አልነበራትም። ወይም እንደ ሁለቱ አገሮች የነገ ተስፋ የሚታይባት አገር አልነበረችም። የደህንነቱ ቢሮና ባልደረባው ሻ/ል ተስፋየ ግን እንደ ዶ/ር ኀብልስ ተቀናቃኝ ሃይሎችን በሃሰት ወንጅሎ ለማጥፋት የጎነጎኑትን ሴራ እውነት ለማስመሰል ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳን አለ ቦታቸው እማኝ ጠርተዋቸዋል። በሻቢያ በኩል የተጠረጠረው ግንኙነትም ከዚህ የተለየ አልነበረም።

"በሻቢያ የታጠቀው ቡድን አሲምባ ሲገባ ብርሃነ መስቀል ዕረዳና አስክንደር ደምሴ በስውር አዲስ አበባ ገብተው ከጀብሃና ከሻቢያ ከነዚህ በስተጀርባ ደግሞ ከአ ልጄሪያ የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ለማከናወን ዝግጅት ጀመሩ" ብለዋል። ሻ/ል ተስፋየ ቀድሞውን ነገር አሲምባ የገባውን የኢሕአሠ ጥንስስ ሻቢያ አላስታጠቀውም። ስልጠናውንም ሆነ ትጥቁን የተቀበለው ከፍልስጤም ነፃ አውጭ ድርጅት እንጂ ከሻቢያ አልነበረም። ኢሕአፓ በከተማ የነበርውም ትብብር ከጀብሃ ፈዳይን ጋር እንጂ ከሻቢያ ጋር አልነበረም። ኀይቶምም የጀብሃ አባል እንጂ ደህንነቱ እንደሚለው የሻቢያ አባል አልነበረም። የጀብሃና የኢሕአፓ የከተማ ትብብርም ከግራዚያኒ መንግስቱ ግድያ ሙከራ ያለፈ እንቅስቃሴ አልተንቀሳቀሰም። የገጠሩ የኢሕአፓና የሻቢያ ትብብርም የደህንነቱ ቢሮ እደሚወነጅለው ኢሕአፓ የሻቢያ ጉዳይ አስፈፃሚነት ሚናና ተልዕኮ አልነበረውም። ቀደም ሲል

የአፄው መንግሥት  በልዑል አስራተ ካሳ በኩል ከሻቢያ ጋር ጀምሮት በነበረው መንፈስ ነበር ኢሕአፓም ግንኙነቱን ከሻቢያ ጋር የጀመረው።

እንደሚታወቀው የልዑል ዐስራተ ካሳና የሻቢያ ግንኙነት ራሱን በራሱ ደብቆ የቀረ ግንኙነት አልነበረም።መንግስት ያውቃል። በወቅቱ ጀብሃ አረባዊና እስላማዊ ሆኖ ስለታየ መንግስት ከክርስቲያኑ ከሻቢያ ጋር በመወገን ዐረባዊውን ጀብሃን በማጥፋት የቀይ ባህርን ከዐረብ ቁጥጥር ነፃ ለማድረግ ነበር። ይልቁንም ከሸዐቢያ ጋር በመደራደር የኤርትራን ጉዳይ ዕልባት በመስጠት አገሪቱን ከመበታተን ለማዳን ታስቦ ነበር ልዑል አስራተ ካሳ ሻቢያን እንዲያሸከረምሙ ሃላፊነቱን የወሰዱት። የኢሕአፓና የሻቢያም ግንኑነት በጀበሃ ርዕዮትና በሻቢያ ማርክሲስት ባህሪይ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ነበር። ኢሕአፓ ከነዚህ አማፂያን ጋር የነበረው ግንኙነትም የደህንነቱ ቢሮ እንደፈበረከው የጌታና የሎሌ ግንኙነት ዐይነት ባህሪይ አልነበረውም። በወቅቱ የአፄው መንግስት፣ ዋሽንገተንና ኢሕአፓ ከሻቢያ የሚፈልጉት የየራሳቸው ጥቅም ነበራቸው።  ሻቢያም ከነዚሁ ሃይሎች ማግኘት የፈለገው ጥቅም ነበረው። ስለሆነም ሁሉም ወገን የየራሱን ጥቅም ለማግኘት ተንቀሳቀሰ። ዋሽንግተንና የአዲስ አበባው መንግስት የሚጋሩት የጋራ ስጋት የጀብሃ ዐረባዊ መሆንና የቀይ ባህር ጉዳይ ነበር። ከዚህም ስጋት ተነስታ ዋሽንግተን አንድ ፕሮጀክት ነደፈች። የዛፍ ተከላ ፕሮጀክት። የፕሮጀክቱ ሃላፊም ሮበርት ካፕላን ሆኖ በፕሮጀክቱ አዲስ አበባም ተሳትፋ በኤርትራ ብዙ ዛፎች ተተከሉ። በራሱ በጀብሃ ውስጥም የአሜሪካ ዛፍ ተተከለ። ዋሽንግቶንና የአዲስ አበባው መንግስት ጀብሃን ለመጥፋት ሲሉ ከሻቢያ ጋር ግኑኝነታቸውን አጠነከሩ። ሻቢያም በሁለቱ እርዳታ እየፈረጠመ መጣ። ሁለቱ መንግስታትም የወል ልጃቸውን መንከባከቡን ቀጠሉበት። በተለይም ልዑል አስራተ ካሳ ከመንግስት ካዝናና ግምጃ ቤት ገንዘብና መሳሪያ እያወጡ ለሻቢያ ሲሰጡ የደህንነቱ ቢሮ ሳያውቀው ነበር ብሎ መገመት ራስን ማሞኘት ይሆናል።ደህንነቱም ይህን ምስጢር ከንጉሡና ከባለስልጣናቱ እውቅና ነስተውት ነበር ብሎ ለማመን ይከብዳል። ልዑል አስራተ ካሳ ከንጉሱ አፍንጫ ስር አዲስ አበባ ውስጥ ተቀምጠው "እኔ ሳላውቀው ምንም ዓይነት ወታደራዊ እንቅስቃሴ እንዳይደረግ" ሲሉ የንጉሱን ፈቃድ ሳያገኙ ነበር ብሎ መገመት ያስቸግራል። የሆነው ሆኖ ግን ሻቢያ በተሰጠው መሳሪያ የዱር አራዊት አላደነበትም። የኢትዮጵያን ወታደር ነበር የገደለበት።

የአፄው መንግስት ተገርስሶ በደርግ ሲተካ ያን አረመኔ ቡድን ለማስወገድ ኢሕአፓም ከሻቢያ ጋር በገጠር የተወሰነ እንቅስቃሴ አድረጎ ነበር። ግንኙነቱም ቀደም ሲል የአፄው መንግስት ከሻቢያ ጋር አድርጎት የነበረው ግንኙነት ካዘለው ዓለማ የተለየ ዓለማ አልነበረውም። ደርግም ቢሆን በሁዋላ ላይ ከጀብሃ ጋር ጀምሮት የነበረው ግንኙነት ከዚህ መንፈስ የተለየ ዓላማ አልነበረውም። ግራም ነፈሰ ቀኝ  ሻቢያ ግን ከዋሽንግቶንና ከአዲስ አበባ ጋር ግንኙነቱን ቀጥሎ ራሱን ካጎለበተ በሁዋላ በጉዲፍቻው በወያኔ ጀብሃን ከጭዋታ ውጭ አደረገው። ቀጣዩ ታዳኝ አውሬም ኢሕአፓ ሆኖ በዋሽንግቶን ቡችላዎች ተነከሰ። የመጨረሻው ጥፊም ደርግ ላይ አርፎ አሁን ለምንገኝበት ሁኔታ በቅተናል። ሻ/ል ተስፋየ ግን የኢሕአፓና የሻቢያ ግንኙት ወሳኝነት ሚና የነበረው ለማስመሰል ጥረዋል። በወቅቱ  ሁሉም ወገን ግኑኝነቱን የመሰረተው የየራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ነበር። ብልጡ ብልጣብልጥነቱን ተጠቅሞ ግቡን መታ። የተበለጡት ተበለጡ። የሚገርመው ግን በወርቅ ሰፌድ ኤርትራን አቅርቦ ለተባበሩት መንገስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ ለግብፃዊው ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ ኤርትራን አስገንጥልልን ያለውን መለስ ዜናዊንና  ወያኔን ሚኒሊክ ቤተመንግስት ውስጥ አስቀምጦ በአሁኑ ወቅት ኢሕአፓን በኤርትራ ጉዳይ መክሰስ ለወያኔ አገልጋይ ከመሆን ሌላ ምን ይሉታል? የሱማሌው ጉዳይስ?

ሻ/ል ተስፈሰዬ ለመፅሐፋቸው የመረጡለት ርዕስ "ምስክርነት ከባለስልጣናቱ አንደበት" የሚል ሲሆን በመፅሐፉ ገፆች የተካተቱት አሳቦች ግን ሙሉ በሙሉ ከባለስልጣናቱ አንደበት የተወሰዱ አይደሉም። ከባለስልጣናቱ መሃል እንዳቸውም ኢሕአፓን በሻቢያ ነገረፈጅነት ሲወነጅሉ አልተስተዋሉም። በሱማሌ ጉዳይም እንዲሁ።ሻ/ል ተስፋዬ ግን እንደ ኤርትራ አማፂያንና ኢሕአፓ ግንኙነት በሱማሌው ጦርነትም  በኢሕአፓ ላይ የተዛባ ትረካ ከኪሳቸው አውጥተው ጨምረዋል። እንደሚታወቀው ከሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ጋር ተያይዞ ሻ/ል ተስፋሰየንና በዓሉ ግርማን ያካተተ

አንድ የቅስቀሳና የፕሮፖጋንዳ ኮሚቴ ተቋቁሞ ነበር። ኮሚቴውም የስራ ክፍፍል ሲያድርግ ሻ/ል ተስፋየ የሱማሌን ጉዳይ በሃላፊነት መውሰዳቸው ይታወሳል። በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በተለይም በወቅቱ በሻ/ል ተስፋዬና በፕሮፖጋንዳው ኮሚቴ ስለ ኢሕአፓ የተባሉ ብዙ ነገሮች ነበሩ። ከተባሉት ጥቂቱ "ኢሕአፓ የሰይድ ባሬ ቅጥረኛ ነው። በጦሩ ቀለብ ደረቅ ስንቅ ውስጥ የተፈጨ አሸዋና የጠርሙዝ ስብርባሪ ጨምሯል። በግንባር የተሰለፉትን አባላቱን (መኮንኖች) ሸሹ በማለት ግንባሩን ለጥቃት አጋልጧል። አምስተኛ እረድፍ........ወዘተ" የሚሉ ይገኙበታል።

ሻ/ል ተስፋዬና ኢሠፓዎች ዐይን ራሱን አያይም እንዲሉ እነርሱ ሌላውን እንደሚወነጅሉት የራሳቸውን ወንጀል ወደ ውስጥ መመልከት ይቸግራቸዋል።ወይም ለማየት አይፈልጉም። ገዳይ ሆነው ቅዱሳን፣ ከሃዲ ሆነው ተአማኒ፣ አምባገነን ሆነው ዴሞክራት፣ አፍራሽ ሆነው ገንቢ፣ አገር ገዳይ ሆነው አገር አልሚ፣ ፀረ-ሕዝብ ሆነው ሕዝባዊ ለመምሰል ኢሕአፓን ያለ ስሙ ስምና ያለ መልኩ መልክ መስጠቱን ሥራየ ብለው ይዘውታል። የአገር ፍቅር በማን ልብ ውስጥ እንደ ቋያ እሳት እንደሚነድ የሚያውቀው የትኩሳቱ መለኪያ ሕዝብ ነው። ሕዝብ ግን ቀደም ብሎ በደርግ አሁን ደግሞ በወያኔ ተረግጦ ስለሚገዛ  ማን ለርሱ ቤዛ እደሆነለት ምስክረነቱን ለመስጠት አንደበቱ ተሸብቧል። የሆነ ሆኖ ግን ለአገር አንድነት የየበኩላችንን ድርሻ በመስዋዕትነት የከፈልን ዜጎች ታሪካችን በገዳዮቻችን ትቢያ ለብሶ ስናይ ምን ያክል ወደ ውስጥ ዘልቆ እደሚነካን የምናውቀው የተበደልነው ወገኖች ብቻ ነን። ኢሕአፓ ከሱማሌው ጦርነት ቀደም ብሎ በደርግ ውስጥ በነበሩት አባላቱ በጀኔራል ተፈሪ ባንቴ በኩል ብሔራዊ ዕርቅ ጠይቆ "ዕርቅ የለም" ያለው መኢሶን ነበር። ከዚያ በሁዋላ ኢሕአፓ ከደርግ ጋር በትብብር ሊያካሂደው የሚችል ነገር እንዳይኖር በሩ ሁሉ ተዘጋበት። በዚህ ወቅት የሱማሌው ጦርነት እየገፋ መጣ። ድርጅቱ የጦርነቱን ሁለንተናዊ ገፅታ ተመልክቶ ጦርነቱ የሕዝብን ጥቅም የሚያስጠብቅ ጦርነት እንዳልሆነ ገመገመ። የግምገማውንም ጭማቂ በአንዲት በራሪ መግለጫ ገለጠ። ቃል በቃል ባይሆንም መግለጫው እንዲህ የሚል ነበር፦

የኢትዮጵያና የሱማሌ ሕዝብ ሆይ ይህ ጦርነት አንድም የሱማሌን አለያም  የትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ ጦርነት አይደለም። ጦርነቱ የሁለቱን አገሮች ሕዝቦች የሚያወድም እንጂ። ስለሆነም የሁለቱም አገር ሕዝቦች ጦርቱን ለማምከን በያሉበት ተቃውሞአቸውን እንዲያጣጡፉ የሚል ጥሪ አቀረበ። በርግጥም ጦርነቱ በሁለቱም ወገን ሲታይ አውዳሚ ነበር። በመሆኑም ጦርነቱ እንዳይጀመር መታገል ክፋት አልነበረውም። እዚህ ላይ በኔ እምነት መግለጫው አንድ ህፀፅ ያለበት ይመስለኛል። ኢሕአፓ የሁለቱን አገሮች ሕዝቦች ጦርነቱን ተቃውመው እዲቆሙ ጥሪ ሲያድርግ  ያልተገነዘበው ነገር የሱማሌን ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርብ ዕርቀት አግኝቶ በተቻለው መንገድ ሁሉ ጦርነቱን እንዲቃወም ተመሳሳይ ቅስቀሳ መስጠት አለመቻሉን በወቅቱ ልብ ያለው አልመሰለኝም። ከዚህ ውጭ ኢሕአፓ ስለ ሱማሌው ጦርነት ሊወቀስበት የሚችል አንድም ነገር አልነበረም። ጦርነቱ እንደተጀመረ የሐረር ዞን ምን እናድርግ? ብሎ ሲጠይቅ ካመራሩ የተሰጠው መመሪያ ከሕዝቡ ጎን ሆናችሁ የመከላከል እርምጃ ውሰዱ የሚል ነበር። በመሆኑም ከማንም በፊት ቀድመው የተሰውት የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ነበሩ። ሻ/ል ተስፋየ ግን የመኢሶንን ቅርሻት እያሸተቱ ኢሕአፓን ይገማኛል ማለት ሰለሚቀናቸው በካድሬነት ዘመናቸው የፃፉትን ወረቀት ፈላልሰው ያገኙትን የፕሮፖጋናንዳ ቅጅ በመፅሐፋቸው አካትተው "ከባለስልጣናቱ አንደበት" የተገኘ ሲሉን ይሉኝታቸው ከድቷቸዋል።

የደህንነቱ ባልደረባ ሻ/ል ተስፋዬ አንገት ለምን ተሠራ? ተብለው ቢጠየቁ ራስን ለመሸከም እንጅ አዙሮ ለማየት ብለው ይመልሳሉ ተብሎ አይጠበቅም። ሲፈጥራቸው አንገት የሚባል ነገር የሠራላቸው አይመስሉም። ይንንም ባህሪይ ሲያስተጋቡ "በኛ አብዮት ሂደት ዕርቅ እንደነውር የታየ ይመስላል። ኢሕአፓና መኢሶን ተነጋግረው ልዩነታቸውን መፍታት አልቻሉም። ገና ለበቀል ታጥቀው እንደተቀመጡ ናቸው። የኢሕአፓ አባላትማ ዳኛ አቃቤ ሕግና ምስክር ሆነው በሰው ትከሻ ቂም ለመወጣት እየተራኮቱ ነው።'አሳፋሪ ተፈጥሮ'! እኔ እንደ ኢሕአፓነቴ ምን ጥሩ መንስ መጥፎ ነገር ፈፀምኩ.......? በማለት ራስን መመርመርና ወደ ህሊና መመለስ የሚያስፈልግ ይመስለኛል" ሲሉ አንገት አላቸው ለማለት ያስቸግራል። ኢሕአፓ ልዩነቶቻችንን

በጠረጴዛ ዙሪያ እንፍታ ሲል በጀኔራል ተፈሪ ባንቲ አመካኝነት ያቀረበውን የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ "ዕርቅ የለም" ብሎ መግደሉን የቀጠለው መኢሶን አልነበረምን? ይህንኑስ ሀቅ ባለስልጣናቱ ደጋግመው እንደነገሯቸው ቀደም ብለው በመፅሓፉ ገፆች አላሰፈሩትምን?

ኢሕአፓ አይደለም በራሱና በመኢሶን መሃል የነበረውን ልዩነት የኤርትራንም ችግር በሰላም እንዲያልቅ ወትውቶ ነበር። ደርግ ግን "በምስራቅ የተገኘው ድል በሰሜንም ይደገማል" በማለት ሰላምንና ዕርቅን ገፍትሮ ሁሉንም ለመደምሰስ በወሰደው እርምጃ የአገሪቱ የቁርጥ ቀን ልጆች በየፈፋው በከንቱ ወድቀው ቀሩ።የ ዕርቅ መጀመሪያው ከራስ ጋር መታረቅ ነው።ሻ/ል ተስፋዬ ግን ከራሳቸው ህሊና ጋር ሳይታረቁ ሌሎችን የዕርቅ ነውረኞች ሊያስመስሉ ጥረዋል። በኢሕአፓ ቤት ዕርቅ እንደ ነውር የታየበት ጊዜ ኖሮ አያውቅም። ኢሕአፓ እንደ ደርግ ወያኔንም ለብሔራዊ ዕርቅ ቀደም ሲል ትግራይ ውስጥ ቀጥሎም ቶሮንቶ ላይ በኢድሃቅ ምሥረታ ከዚያም አዲስ አበባ በጊዎኑ ጉባኤ ለብሔራዊ ዕርቅ ጠርቶት ነበር። ወያኔ ግን በተለይ በጊዎኑ ጉባኤ "እኛ ከማንም ጋር ጠብ የለንም። የተጣሉ ሊታረቁ ይችላሉ" ብሎ ነበር ያሾፈው። ኢሕአፓ ሻ/ል ተስፋዬ እንደሚወነጅሉት ለበቀል ታጥቆ የተቀመጠ ድርጅት አይደለም። ለብሔራዊ ዕርቅ ያለውን ቅንነት ከኢሠፓና ከመኢሶን ጋር በኢድሃቅና በኢድሃህ የሕብረት ግንባሮች አስመስክሯል። ዛሬም ድረስ "ዕርቅ የለም" የሚሉት የኢሠፓ ርዝራዦች እንጅ ኢሕአፓ አይደለም። ኢሕአፓ ከድርጅታዊ ክብሩና ጥቅሙ ይልቅ አገሩ እንደምትበልጥበት አውቆ የትናንት ገዳዩን መኢሶንን በኢድሃቅና በኢድሃህ የህብረት ግንባሮች ተሸክሞት ብዙ ጎዳና እንደተጓዘ ሻ/ል ተስፋዬ አጥተውት አይመስለኝም "ገና ለበቀል ታጥቀው እንደተቀመጡ ናቸው" የሚሉን።

"የኢሕአፓ አባላትማ ዳኛ አቃቤ ሕግና ምስክር ሆነው………" ሲሉ አሁን ማን ይሙት ብአዴን ኢሕአፓ ሆኖ ነው ብአዴን ላይ ያላቸውን ቅሬታ ኢሕአፓ ላይ የሚለጥፉት? "እኔ እንደ ኢሕአፓነቴ ምን ጥሩ ምንስ መጥፎ ነገር ፈፀምኩ?…… በማለት ራስን መመርመርና ወደ ህሊና መመለስ" ሲሉስ እርሳቸው የራሳቸውን ህሊና ቀድመው መርምረውና ወደ ህሊናቸው ተመልሰው የበደሉትን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቀው ይሆን ሌሎቻችንን የሚወቅሱን? ራሳቸውን ሳይወቅሱ ሌላውን ለመውቀስስ የሞራል ብቃት እንደሌላቸው ሻምበሉ ይገነዘቡት ይሆን?

ሻ/ል ተስፋዬ ስም በማጥፋት እንደ ናዚዎች የተካኑ ይመስላሉ። ናዚዎች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአይሁዶች ላይ የጀመሩት ፀረ-አይሁድ ዘመቻ ወደ ሩሲያም ተሸጋግሮ የሩሲያ አይሁዶችም በሕዝብ ዘንድ እንዲጠሉ በተጀመረው ፕሮፖጋንዳ በመንገዶች፣ በመኪኖች ውስጥ፣ በሥራ ቦታዎች፣ እንዲሁም በገበያ ስፍራዎች የሚወሩት ወሬወች በሞስኮው አካባቢ የሚገኙ የመዳህኒት ቤቶች (ፋርማሲዎች) የተዘጉት ባለቤቶቹ የአሜሪካ-ሰላዮች አይሁዶች የደረቀ ቅማል በኪኒን መልክ ሲሸጡ ስለተያዙ ነው ተብሎ ይወራ ነበር። በማዋለጃ ቤቶች የሚወለዱ ፅፃናትና እናቶችም በቂጥኝ በሽታ ተለክፈው ይወጣሉ፡ በጥርስ ህክምና ጣቢያዎች የጥርስ ቀዶ ጥገና ሃኪሞች የመንጋጋና የምላስ ነቀርሳ መርፌ ይወጋሉ። ሌላው ቀርቶ የክብሪት ሳጥኖች በውስጣቸው የያዟቸው እንጨቶች በመርዝ ተሞልተው ባልባሌ (በማይጠረጠሩ) ሰዎች አማካኝነት ወደ ሕዝብ ተሰራጭተዋል የሚል ወሬ በስፋት ተነዝቶ ነበር። ዛሬ በኢሕአፓ ላይ የሚነዛው አሉባለታም አይሁዶች በዚያን ወቅት በህዝብ ተጠልተው የደረሰባቸውን ግፍ ዓለም በዝምታ ትመለከተው እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አማራና ኢሕአፓ በዘመናይ ባለቀኖች እንደ ያኔው አይሁዳዊያን የሚደርስባቸውን ግፍና ጭፍጨፋ ዓለም በዝምታዋ እያጀበችው መሆኑን እየታዘብን ነው። ነገር ግን "ሁሉም ነገር ያልፋል። የማያልፈው ጊዜ ነው።ሁሉም ነገር ሲኖር እርሱ ብቻ ያልፋል። በጊዜ ስሌት ቆሞ የሚኖር ነገር የለም። ጊዜው ሲኖር ይኖራል ጊዜው ሲያልፍም አብሮ ያልፋል" እንደተባለው አይሁዶች ቀናቸው ያለቀባቸውን ናዚዎች ፍትህ አልነፈጓቸውም። የወያኔ ቀንም ሲያልቅ ወያኔና ኢሠፓ እንደ ናዚዎች ፍትህ ይቸራቸዋል። ሁለቱ ፀረ-ሕዝብ ሃይሎችም ይህንኑ አይቀሬ ፍትህ ከመፍራት አኳያ ይመስላል

"አትርሳው በደልክን አንቆርቁረው በቅል

**ነቀዝ እንዳይበላው ለከርሞ እንዲበቅል“**
**እንዲሉ ነገ ኢሕአፓ ወደ ስልጣ ከመጣ ለፍርድ ያቀርበናል ከሚል ስጋት ተንደርድረው በኢሕአፓ ላይ የተቀናጀ  ዘመቻ ከፍተዋል። “ነገ ሌላ ቀን ነው“ እንደተባለውም  ነገ የኢትዮጵያ መንግሥት ሲቋቋም ከእያንዳንዱ እንደየ በደሉ ለእያንዳንዱ አንደየ ሥራው ፍትሁ ይከፈለዋል። ሉሁሉም ግን የዚያ ሰው ይበለን።**

**october19,2009**
**abraham  beyenne**